የደቀ መዝሙርነት መርሖዎች

# የክርስትና ሕይወት መርሖዎች

## የጥናት መመሪያ

## የወንጌል ሥርጭት መንደርደሪያ

### ትምሕርት 1፥ ዓለምን በወንጌል የመድረስ ጥሪ

## መግቢያ

ይህ ትምሕርት ከደቀመዝሙርነት መርሖዎች የትምሕርት መድብሎች አንዱ አካል ሲሆን፣ ርዕሱም | ርዕሱም “የወንጌል ሥርጭት መንደርደሪያ” የሚል ነዉ። የዚህ ተከታታይ ትምሕርቶችን ያቀፈው ክፍል ዓላማ፣ ተሳታፊዎች ወንጌልን በብቃት ለሌሎች በማካፈል (በማሠራጨት) ዉጤታማ እንዲሆኑ፣ ማስታጠቅና ማዘጋጀት ነዉ። እግዚአብሔር ለአገልግሎት (ለሚኒስትሪ) እንዴት እንደሚያስታጥቀን መረዳት፤ የወንጌል መልእክታችንን፥ ለተለያዩ የዓለም እይታ ወይም አመለካከቶች እንዴት እንደምናዘጋጅ እናስተዉላለን። ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ዉስጥ የተገኘዉንና፤ የማይለወጠዉን የተስፋ መልእክት፥ ወይም የምሥራች ቃል፤አሁንም ገና ክርስቶስን ወደ አላወቀዉ ዓለም እንድናመጣ ይረዳናል።

የጥናት መመሪያዉ ዓላማ ግለሰቦች የተለያዩ ትምሕርቶችን እያንዳንዳቸዉን በተናጠል ወስደዉ በጥልቀት እንዲመረምሩና በግላቸዉ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለመርዳት ነዉ። ይህን ትምሕርት ከሌሎች “የደቀመዝሙርነት መርሖዎች” ማቴሪያሎች፥ ማለትም፥ ጽሁፎች፥ ኦዲዮ፥እና ቪዲዮ ዉጤቶች ጋራ በጥምረት መጠቀም ይቻላል።
በድረ፡ገፃችን፥ www.DEamharic.org ይመልከቱ።

---

ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ1954 ዓም ከታተመዉ የድሮዉ (KJV) ትርጉም ሲሆን፥ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፈቃድ ተቀድተዉ የታተሙ ናቸዉ።

ሌሎች ሁሉም ይዘቶች የ © 2019 ትራንስ ዎርልድ ራዲዮ ካናዳ ነው። ይህንን ግብአት ለመጠቀም ዋጋ እስካልጠየቁ ድረስ እና ስለ ክርስቶስ አለምን መድረስን አላማዎ አድርገዉ እስከሰሩ ድረስ በፈለጉት አይነት መንገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ተጨማሪ የፍቃድ ዝርዝሮችን በ www.discipleshipessentials.org/ licensing ይመልከቱ.

# የወንጌል ሥርጭት መንደርደሪያ
## ትምሕርት 1፥ ዓለምን በወንጌል የመድረስ ጥሪ

### የትምሕርቱ ትኩረት?

ሰዎች በሕይወታቸዉ ያለዉን ዓላማ ለማወቅ፣ በመገረም አዘዉትረዉ ይጠይቃሉ። ለመሆኑ እግዚአብሔር የሕይወታችንን ዓላማ በቃሉ ዉስጥ፥ ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ እንደገለጠልን አስተዉለሃልን? ይህ ትምሕርት፥ ከእግዚአብሔር ጋራ ኅብረት በማድረግ፣ እርሱ ለሕይወትህ ያለዉን ዓላማ ለማከናወንና ገፍፃሜ ለማድረስ ስትዘረጋ፤ አስቀድመህ የእይታህን ማዕዘን ወይም አመለካከት ህን፣ ከእግዚአብሔር አተያይ ጋራ እንድታጣጥም ይረዳሃል።

### ፈጣን ግንዛቤ…

ይህ ትምሕርት:- እያንዳንዱ ክርስቲያን በወንጌል ሥርጭት ላይ እንዲሰማራ፥ ያለዉን ዓላማ ይመረምራል። ወንጌል ሥርጭት ስንል:- የመንጌልን መልእክት ለሌሎች ማካፈል፥ መመስከርን፤ ለመግለፅ የምንጠቀምበት ቃል ነዉ፤ ማለትም ለኃጢአታችን ሥርየትን አግኝተን፣ ከአብ አባታችን ከእግዚአብሔር ጋራ መታረቅ የምንችለዉ፤ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ብቸኛዉ መንገድ የመሆኑን፣ መልካም ዜና ወይም፥ የምሥራቹን ቃል ማብሰርን ያመለክታል። በወንጌል ሥርጭት ላይ መሰማራት፣ የሥራ መደባችን እና የሕይወታችን አቅጣጫ የተለያየ ቢሆን እንኳን፣ ሁላችንም የተጠራንበት ሥራ ነዉ። አንዳንድ ጊዜ ግን:- ለምን እንደ ተወለድን፣ በሕይወት ዉስጥ ዓላማችን ምን እንደሆነ፣ ወይም እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ ምን እንድንሰራ ይፈልጋል፣ የሚሉት ሃሳቦች በጣም ያስደንቁናል። ለዚህ ጥያቄ ብቸኛዉ መልስ፣ ለእያንዳንዱ ሰዉ የተለያየ መሆኑን ያሳያል። የተወሰኑት ለሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ይጠራሉ፤ አብዛኞቹ ግን፥ ሌሎች ሥራዎችን እየሠሩ በሚያገኙት ገቢ ቤተሰባቸዉንና የገንዘብ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸዉን ወገኖች እየረዱ፤ ከእግዚአብሔር በተቀበሉአቸዉ ስጦታዎች ደግሞ ቤተ ክርስቲያናቸዉንና፣ ማኅበረሰቡን ለማገልገል ጥሪ ያላቸዉ ናቸዉ። በመሠረቱ፥ የትኛዉም የሕይወት እርከን ላይ ያለ፤ ማንኛዉም ሰዉ:- በዙሪያዉ ያለዉን ዓለም፣ ጎረበቶቹን፣ እርቀዉ ያሉትንም ሳይቀር፣ ሕይወትን ለዋጭ የሆነዉን የወንጌል መልእክት ይዞ ሊደርሳቸዉ ይችላል።

# እንጀምር

**1.** በሆነ አጋጣሚ፥ አንድ ሰዉ:- “በዚህ ዓለም ዉስጥ የእግዚአብሔር ዓላማ ምንድን ነዉ” ብሎ ቢጠይቅህ፣ ምን ብለህ ታስረዳለህ?

**2.** አንተን ቀርቦ፣ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እንድትመጣ፣ የረዳህ ሰዉ ነበረ? ለመሆኑ አንድ ሰዉ ወንጌልን መስክሮልህ ያዉቃልን? ይህ ከሆነ፥ የክንዋኔዉ አኳኋን ምን ይመስል ነበረ?

# ጥናት

## 1. የሰዉ ልጅ ዓላማ እና፥ የእግዚአብሔር ዓላማ

እያንዳንዳችን የተለያዩ የሕይወት ገፅታዎች አሉን፥ የሉንም እንዴ? የቤተሰብ ሕይወታችን፣ የሥራ ሕይወታችን፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ፥ የትምሕርት ሕይወታችን፣ ወይም ደግሞ፡- በስፖርት፥ በዝንባሌ ተሳትፎ (Hobby)፥ ወይም በፈጠራ ክትትል ዙሪያ፣ የሚሽከረከር የሕይወት ገፅታ ይኖረናል። ሌላዉ ደግሞ መጠነ ሰፊዉ የክርስትና ሕይወታችን ነዉ። የተወሰኑ ሰዎች፥ ይኸኛዉ የእምነት ሕይወታችን፥ ከሌሎቹ የሕይወታችን ገፅታዎች የሚጋራዉ እጅግ ጥቂት ነዉ ወደሚለዉ ሃሳብ ያዘነብላሉ። በእርግጥም፥ ከምናደርገዉ የእግዚአብሔር አምልኮ የተለዩ ለሚመስሉት፤ የቤተሰብ እና የሙያ ሕይወታችን፣ ዓላማ እና ግብ ሊኖረን ይችላል። ዳሩ ግን፥ በሕይወት ዉስጥ ያለን ዓላማ፡- ኃብትና ንብረት ማጠራቀም፣ወይም ኃይል፥ሥልጣን እና ዝናን መቀዳጀት ነዉ፣ ብሎ መወሰን ፈታኝ ሊሆን ይችላል። ለነገሩ እነዚያ ነገሮች ደኅንነትንና ደስታን ሊያስገኙ ይችላሉ፤ ነገር ግን፥ ሕይወታችን በምን ዙሪያ ማማከል እንደ አለበት፣ መጽሐፍ ቅዱስ የተለየ ዓላማን ያሳየናል። የእግዚአብሔር ዓላማ ግን፡- እግዚአብሔርን በማክበርና ከፍ ከፍ በማድረግ፤ የራሳችንን የግል ዓላማ ወደ ጎን ጥለን፣ በምትኩም እግዚአብሔር ለእኛ ያለዉን ዓላማ አንስተንና ከፍ አድርገን፤ በየትኛዉም የሕይወታችን ገፅታ እርሱን እንድናገለግል ነዉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረበት ጊዜም ቢሆን፣ ሰዎች ኃብትና ሥልጣንን ወድደዋል፥ ተከትለዉትማል። ጌታ ኢየሱስ ሁላችንም ከራሳችን ጋራ በማዛመድ ልናመሳክር የምንችለዉን ታሪክ የተናገረዉ፡-ሉቃስ 12:16–20 ዉስጥ ሰፍሮ እናገኛለን።

- ❖ ሉቃስ 12:16–20 ን ከመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ፈልገህ አንብብ። የተፈፀመዉንም ገልፀህ በፅሑፍ አስፍር።

| |
|---|
| |

- ❖ ከላይ የቀረበዉን ታሪክ አስተዉልና፡- በታሪኩ ውስጥ ያለዉ ሰዉ ያተኮረበትን፤ የእግዚአብሔር ትኩረት ከሆነዉ ነገር ጋራ አነፃፅረዉ። እያንዳንዳቸዉ ከሁሉ አስፈላጊ ነዉ ብለዉ የወሰኑት ምን ነበር?

| ሰዉየዉ | እግዚአብሔር |
|---|---|
| | |

ነፍሳችን የመንፈሳዊዉ እኛነታችን አካል ናት። ለመሆኑ ነፍስ ለእግዚአብሔር እጅግ ጠቃሚና አስፈላጊ የሆነችዉ ለምንድን ነዉ? ነፍሳችን፡- ከእግዚአብሔር ጋራ፣ ወይም ደግሞ ከእርሱ ተለይታ፣ ለዘላለም የመኖር (ዘላለማዊ) ተስፋ አላት። ስለሆነም፥ የእግዚአብሔር ፍላጎት፥ ሰዎች ለኃጢአታቸዉ ንስሐ ገብተዉ ምኅረትን እንዲያገኙና፤ ነፍሳቸዉም ከእርሱ ጋራ ለዘላለም እንድትኖር ነዉ። ምን ያህል ታላቅ እና ድንቅ ቢሆን፣ ከአንዲት ነፍስ ጋራ ሊስተካከል የሚችል፣አንዳችም ኃብት ወይም ንብረት አይኖርም!

## 2. ዓለምህን በወንጌል የመድረስ ጥሪ

❖ የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብና፤ በዓለም ዉስጥ የእግዚአብሔር ቀዳሚ ዓላማ ምን እንደሆነ መርምረህ ተረዳ። በጥናትህ የተገነዘብከዉንም በፅሑፍ አስፍር።

| | |
|---|---|
| ሉቃስ 19:10 | |
| ሮሜ 10:9,10 | |

በጽሐፍ ቅዱስ የሰዉን ልጅ ዓላማ በግልፅ ያብራራልናል። ይህም እዉነታ እያንዳንዱን ሰዉ ይመለከታል።

❖ በእነዚህ ጥቅሶች ዉስጥ፣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቁልፍ ትእዛዛት ምንድን ናቸዉ?

| | |
|---|---|
| 1ኛ ቆሮንቶስ 10:31 | |
| ማቴዎስ 28:16–20 | |

ይህ በሚያስገርም ሁኔታ አስደሳችና አጓጊ ነገር ነዉ፥ አይደለም እንዴ? የእግዚአብሔር ዓላማ ትልቅ ነዉ፥ አጓጊ ነዉ፥ የዓላማዉም አካል እና፥ ትጉህ ተሳታፊ እንድትሆን ይፈልጋል! ይህም ዓላማ "ታላቁ ተልእኮ" ይባላል። ከላይ ባነበብነዉ በማቴዎስ ወንጌል ጥቅስ በስተ መጨረሻ፣ የሆነ ልዩ ነገር ልብ ብለሃል?

❖ ማቴዎስ 28:20፦ የተሰጠንን ተልእኮ እየፈፀምን ሳለን፣ ከእኛ ጋራ የሚሆነዉ ማን ነዉ ይላል?

| |
|---|
| |

## 3. እግዚአብሔር ያስታጥቀናል

እግዚአብሔር አብረን እየሠራን እንኳን ቢሆን፣ ይህንን ተልእኮ ያለ እርሱ ድጋፍ፥ በራሳችን ብቻ እንድንወጣዉ አይጠብቅብንም! እግዚአብሔር በዙሪያችን ለሚገኙት፣ ከዚያም አልፈን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ፣ ወንጌልን እንድናሰራጭ ለእያንዳንዳችን ትልልቅ ዓላማዎች አሉት!

❖ ዓላማዎቻችንን በአግባቡ እንድናከናዉናቸዉ፤ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያስታጥቀን፣ የሚከተሉት ጥቅሶች ምን ያወሳሉ?

| | | |
|---|---|---|
| ዕብራዉያን 13:21 | | |
| ሐዋርያት 1:8 | | |

❖ ይህንን እገዛ ከእግዚአብሔር ለመቀበል፥ የእኛ ኃላፊነት ምንድን ነዉ? የሚከተሉትን ጥቅሶች አንብብና፥ ስለ ኃላፊነታችን ምን እንደሚል በፅሑፍ አቅርብ።

| | |
|---|---|
| ዮሐንስ 15: 5 | |

❖ አንድ ሰዉ ይህንን እንዴት ይፈፅመዋል ብለህ ታስባለህ?

| |
|---|
| |

ከእግዚአብሔር ጋራ የዚህ ዓይነት ግንኙነት ለምን ያስፈልገናል? እግዚአብሔር እንድናገለግለዉና፥ ለእኛ ያለዉንም ዓላማ ለማሟላት እንችል ዘንድ እንዲያስታጥቀን፡- ሥራዉን የማከናወን ችሎታ፥ አስፈላጊዉን ጥንካሬ፥ ጥበብ እና፥ መረዳት (ግንዛቤ) ከእግዚአብሔር መቀበል ግድ ይሆናል። ይህንን ታላቅ ዓላማ ለመፈፀም ደግሞ፤ ኃያሉና ታላቁ አምላካችን፥ እግዚአብሔር እንዲያስታጥቀን ያስፈልጋል!

ለእግዚአብሔር ቅርብ ሆኖ ለመቆየት፣ ልታከናዉን የሚገቡህ ሦስት ድርጊቶች፡-

- በየዕለቱ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት
- በየዕለቱ አመቺ ጊዜ ለይቶ መፀለይ
- ከሌሎች አማኝ ክርስቲያኖች ጋራ በቋሚነት ጊዜ ማሳለፍና ኅብረት ማድረግ

ከእግዚአብሔር ጋር ለመቀራረብ እንዲረዱህ፣ ማዳበር ያለብህ ሦስት ጠባዮች ወይም አመለካከቶች፡-

- ለሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ላይ መደገፍና በእርሱ ከለላ ሥር  መሆን
- እግዚአብሔርን አመስጋኝ መሆን፤ በእርሱም ደስተኛነትህን መግለፅ
- ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት ፈፅሞ ታዛዥ መሆን

## 4. የእኔ ዓላማ ምንድን ነዉ?

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አማኝ ከሆንክ፤ በእርግጥ ዓላማህ ተገልጦልሃል። እሱም ክብርን ለእግዚአብሔር ማምጣት፣ በእቅዱም መሳተፍና መታዘዝ ነዉ። የእግዚአብሔር እቅድ፥ ቀዳሚዉ ቤዛነቱ ሲሆን፤ ባሕርያቱን እና ኀልወቱን፡- ማለትም ፍቅሩን፥ ፀጋዉን እና፥ ምሕረቱን ገልጦ ማሳየት ነዉ። ይሁን እንጂ፥ ዓላማችን መሆን ስለሚገባዉ እዉነታ፥ የሰዉ ልጅ ያለዉ እይታ እጅግ የተለየ ነዉ። ሰዎች ግን እነርሱ ሲሞቱ በንነዉ የሚጠፉትን፡- የተትረፈረፈ ኃብት ወይም ብልፅግናን፥ ኃይልና ሥልጣንን አብዝተዉ ይሻሉ። አንተስ? ለመሆኑ፥ ሕይወትህን እግዚአብሔር በአንተ ላይ ለአለዉ ዓላማ በማስረከብ፤ ገና ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የማያዉቁትን በወንጌል የምሥራች ቃል፣ በቁርጠኝነት ለመድረስ ተዘጋጅተሃልን?

## ማጠቃለያ

- ❖ ይህ የሕይወት ዓላማዬ ነዉ ብለን የምናምነዉ ነገር፤ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ከአለዉ ዓላማ ጋር፣ አንድ ዓይነት ላይሆን ይችላል።
- ❖ የእግዚአብሔር ዓላማ በምድር ላይ፡- ቅጣት የተገባቸዉን እና ከእርሱም ከአምላካቸዉ ለዘላለም ሊለዩ የተዘጋጁትን ነፍሳት ለማዳን ነዉ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ አብ አባቱ ለእርሱ ከዓለዉ ዓላማ ጋራ ራሱን አስተካክሎ አጣመረ፤ እኛም በበኩላችን፥ እግዚአብሔር ለእኛ ያለዉ ዓላማ፡- ወደዚህ ተልእኮ ዉስጥ ገብተን ተካፋይ እንድንሆን፣ የጠራን መሆኑን እናዉቃለን።
- ❖ አንድ አማኝ ክርስቲያን፥ በየዕለቱ የሚኖርበትን የምድራዊ ሕይወቱን፤ ከመንፈሳዊ ጥሪዉና አገልግሎቱ መለየት ወይም ከፋፍሎ ማየት አይችልም። በሚያደርጋቸዉ በማናቸዉም ነገሮች ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብርን መስጠት ይገባዋል
- ❖ እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገዉ ጥሪ፡-የወንጌልን የምሥራች ቃል እንሰብክና እናሠራጭ ዘንድ፤ ወደ ሰዎች ሁሉ በመሄድ ደቀ መዛሙርት እንድናፈራና እንድናበዛ ነዉ።
- ❖ ለእግዚአብሔር እጅግ ቅርብ በሆንን መጠን፤ ለዚህ ታላቅ ሥራ ያስታጥቀናል!

## ነፀብራቅ ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ለአንተ ሕይወት ያለዉ ዓላማ፣ ከአንተ ዓላማ ጋራ የሚጣጣመዉ እንዴት ነዉ? ሁለቱን ዓላማዎች ለማቀናጀትስ ምን ማድረግ ትችላለህ?

2. ለሌሎች ሰዎች በመመስከር ተልእኮ ወቅት የሚያጋጥሙህ ተግዳሮቶች ምን ምንድን ናቸዉ? እነዚያንም ተግዳሮቶችና ችግሮች የምትወጣዉ እንዴት ነዉ?